

# ዮሴፍ

- ያዕቆብ 12 ልጆች ነበሩት። ከሁሉም አስበልጦ የሚወደው ልጁ ግን ዮሴፍ ነበር። ይህንንም ለዮሴፍ የነበረውን ፍቅሩን ለማሳየት ልዩ ልብስ ገዝቶ በስጦታ አበረከተለት። በዚህ ምክንያትም የዮሴፍ ወንድሞች በዮሴፍ ላይ በጣም ቀኑበት።

- አንድ ቀን ያዕቆብ የወንድሞቹን ሁኔታ አይቶ እንዲመጣ ዮሴፍን ላከው። እስከዚህ ሰዓት ድረስ በዮሴፍ ልብስ ምክንያት ቁጣቸው ስላልበረደላቸው ዮሴፍን በጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። ከዚያም ኮቱን በፍየል ደም ውስጥ ነክረው ለአባታቸው ወሰዱለት። ያዕቆብም ይህን ሲመለከት ልጁን አውሬ እንደገደለበት አሰበ። ወንድሞቹ ዮሴፍን ወደግብፅ ሲጓዙ ለነበሩ ነጋዴዎች ባሪያ ይሆን ዘንድ ሸጡት።

- ዮሴፍ በግብፅ ምድር ውስጥ እያለ ፈርኦን ተብሎ የሚጠራው የግብፅ ንጉስ ሁለት ሕልሞችን አየ። በመጀመሪያ ያየው ሕልም ከወንዝ ውስጥ ስለወጡ ሰባት ወፋፍራም ላሞችና ሌሎች በጣም ቀጫጭን ላሞች ነበር። ቀጫጭኖቹ ላሞች ወፋፍራሞቹን ላሞች በሏቸው ነገር ግን መጠናቸው ምንም አልጨመረም።

- ቀጥሎ የተመለከተው ሕልም ደግሞ ሰባት ያማሩና የሰቡ እሸቶችንና ሌሎች ሰባት በጣም ቀጫጭን አስቀያሚ እሸቶችን ነበር። ሰባቱ ቀጫጭን እሸቶች በጣም የሚያማምሩትንና ወፋፍራሞቹን እሸቶች በሏቸው። የንጉሱን ሕልም ሊፈታ የሚቻለው ማንም አልተገኘም። እግዚአብሔር ግን ለዮሴፍ ሕልሙን የሚረዳበትን ጥበብ ሰጠው።

- ዮሴፍም ንጉሱን እንዲህ አለው፣ ‘በመጀመሪያ ሰባት የጥጋብ አመታት ይኖራሉ። ቀጥሎም ሌሎች ሰባት የድርቅ አመታት ይሆናሉ።’ ከዚያም ዮሴፍ ንጉሱን አንድ አስተዋይ ሰው እንዲመርጥና ሕዝቡን በሚገባ እያስተዳደረ ለድርቁ አመታት በቂ እህል እንዲያከማች መከረው።

- ፈርኦንም አንድ የሚያውቀውን ጠቢብ ሰው መረጠ። እርሱም ዮሴፍ !

ይህ የዮሴፍ ታሪክ በመፅሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት መፅሐፍ ምዕራፍ 37፣ 39 ፣ 40 ፣ እና 41 ላይ ነው።

http://gardenofpraise.com